# የአማራ ወላድ እናቶችን የማምከንና ዘር የማጥፋት ወንጀል በአማራ — ባህር ዳር

(አያሌው መንበር)




የባህር ዳር ጤና ጣቢያ እናቶችን በግዳጅ የ5 ዓመት የወሊድ መከላከያ እየሰጠ ነው፡- ተጠቃሚ ባህር ዳር ቀበሌ 03 ሙሏለም አዳራሽ ጀርባ ያለው ጤና ጣቢያ የአጭር ጊዜ የወሊድ መቆጣጠሪያ (በተለይም የ3 ወር) አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ተቋርጦ የ3 ዓመትና የ5 ዓመት ብቻ እየተሰጠ መሆኑን የአገልግሎቱ ፈላጊ እናቶች መረጃውን አድርሰውናል።

እነዚህ እናቶች እንደሚሉት ሴቶች የወሊድ መቆጣጠሪያ ለመዉሰድ በሚመጡበት ጊዜ የ3 እና የ5 ዓመት ነዉ መዉሰድ /መርፌ መወጋት / ያለባችሁ እየተባሉ በግዴታ አብዛኞችን እየወጓቸዉ ነዉ። እነርሱ ግን የ3 ወር ነዉ የምንፈልገዉ በማለት ሲከራከሩ መመልከቱን ደግሞ ሌላ ሰው አረጋግጦልኛል። ይህ ግለሰብ እንደሚለው ግማሾቹ ባሌ ይቆጣል ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ አንፈልግም እያሉ ሳይወጉ ሚሄዱም አሉ፡፡

በጣም ሚያሳዝነዉ ግን በጣም ብዙዎቹ “የመንግስት አቅጣጫ ነዉ እያሉ በግድ ይወጋሉ። ስለዚህ ለሚመለከተዉ አካል አድርሱ ይላሉ እነዚህ ታዛቢዎችና የአገልግሎቱ ፈላጊዎች።

የአማራ እናቶች የረጅም ጊዜ የወሊድ መከላከያ እንዲወስዱ ከመገደዳቸው ባለፈ የማምከኛ መርፌ ተወግተው ልጅ መውለድ እንዳልቻሉ ከአመታት በፊት ፀበል ተጉዘው ፈጣሪያቸውን እየለመኑ ያሉ በጎጃም የአንድ አካባቢ እናቶችን ሮሮ በቪዲዮ መመልከታችን ይታወሳል።